# « ዲያስፖራ የጦቢያ ሲሦ መንግሥት !!! »

## «ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር፤ »

April 18, 2018




የማይነጋ ሕልም ሳልም
የማይድን በሽታ ሳክም
የማያድግ ችግኝ ስከረክም<
እኔ ለእኔ ኖሬ አላውቅም፡፡"

በዓሉ ግርማ ኦሮማይ

ለኢትዮጵያ ሃገራዊ ንቅናቄ፣ ለኢትዮጵያዊያን የጋራ ግበረ ኃይል፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ፣ ለኢትዮጵያውያን ተጋሩ፣ ለሁሉም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራቶች፡- ሲሦ መንግሥት መሆናችሁን እወቁ!!! የኢትዮጵያዊያን የጋራ ግበረ ኃይል የውጭ ሃዋላ እቀባ አስተባባሪዎች ለወያኔ ጥይት መግዣና መግደያ ዶላር በማሳጣታችሁ እንዲሁም የኤች አር 128 እንዲፀድቅ የታገላችሁ ውድ የሃገራችን ዲያስፖራ ወገኖች የከበረ ምስጋና ይገባችሆል!!! ‹‹የኢትዮጵያ የቦህር ማዶ ዜጎች የኢትዮጵያ ሲሦ መንግሥት ናቸው!!! በህብረ-ብሄራዊ የሃገር ፍቅር ስሜት ለወገናችሁ ገንዘብ እየላካችሁ የምታስደዳድሩት ወገን ብዙ ነው፡፡ ዲያስፖራው ወገን በተለያዮ የሃገር ግንባታ የኢኮኖሚ ዘርፎች በሚተፍ እውቀታቸውንና ገንዘባቸውን በማፍሰስ በግብርና ዘርፍ ፣ በማኑፋክቸሪንግ (ብዙ ፋብሪካዎች የጨርቃጨርቅ፣ የቆርቆሮ፣ የገነቡ )፣ በአገልግሎት ዘርፍ (ሆስፒታልና ፋርማሲ፣ የመድሃኒት ፋብሪካዎች)፣ በሪል ስቴት ቤት ግንባታ ዘርፍ፣ በባንክና ፋይናንስ ዘርፍ (የአዋሽ ባንክ የመሠረቱ የተከበሩ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ፣ የህብረት ባንክ አቶ እየሱስወርቅ ዛፉ፣ የዘመን ባንክ አቶ ኤርሚያስ አመልጋ (አራት አይና የሳይንስና ቢዝነስ፣የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጅ ዘመን ብሩህ ህሊናን ያላቸው ወያኔ መንግሥት አላሰራ ያላቸው ሁሉም ከባህር ማዶ የመጡ የዲያስፖራ ወገኞች ናቸው)፣ በሆቴልና ቱሪዝም (ብዙ ሆቴሎች በየክልሎቹ ገንብተው ጎብኝዎችን በመሳብ የተሰማሩ ብዙ የዲያስፖራ ወገኖች አሉ)፣ በኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጅ ዘርፎች በመሰማራት ሃገር ገንብተዋል፣ ድርሻቸውን የተወጡ ለዜጎች የስራ ዕድል የፈጠሩ፣ የገቢ ምንጭ የፈጠሩ፣ የውጪ ምንዛሪ ያስገኙ፣ በየዮኒቨርሲቲዎቹ በበጎ ፍቃደኝነት መትተው የሳይንስና ቴክኖሎጅ የዕውቀት ሽግግር ያደረጉ ምሁራኖች (ዶክተር ዮናስ አድማሱና፣ ዶክተር ገብሩ መርሻ፣( ሁለቱንም ነፋሳችሁን ይማር)፣ ዶክተር ዳኛቸው አሰፋ፣ ፕሮፊሰር ገብሩ ታረቀ ወዘተ ) ሃገር ቤት ገብተው ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል፡፡ በአንፃሩም በመጥፎ አድርባይ ሥነምግባራቸው ፕሮፌስር አንድሪስ እሸቴ፣ አንተር አፍሪካው አብዱል መሃመድ፣ ዘመዴነህ ፣ ዳዊት ገብረእግዜብሄር የሚሣሡሉት መጥቀስ ግድ ይላል፡፡ ወገናቸውን የሚወዱ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ ፕሮፌስር መሣይ መኮንን፣ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ፣ ፕሮፌስር አለማየሁ ገብረማርያም፣

አቶ ገብረመድህን አርዓያ፣ አለምፀሃይ ወዳጆ፣ ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ርዕዮት ዓለሙ የመሳሰሉት ዲያስፖራ የዜጋዎቻችን የደም ስሮች፣ የአገር ወራጅና ማገር አጥንታችን፣ የእውቀታችን መጋቢና መንፈሳችን ፀጋ የዓለማችን አምዳዊና አግድማዊ ተቆጣጣሪ ልሂቃን ክብርና ሞገስ ለእናንተ ይሁን እንላለን፡፡ የሃገራችን ዲያስፖራ ለአንድ ሶስተኛ ህዝብን ቀለብ ሠፋሪዎች በመሆናቸው፣ በሃዋላ ከሦስት እስከ አራት ቢሊዩን ዶላር በመላክ ሲሦ መንግስት በመሆናቸው ስለሃገራቸው ጉዳይ ከማንም በላይ ከወያኔ መንግሥት በላይ ያገባቸዋል፡፡ የ 2010 ዓ/ም የሃገሪቱ 14 ቢሊዮን ዶላር በጀት ነበር የጸደቀው፣ ከዲያስፖራ የተላከው 4 ቢሊዮን ዶላር ነበር ይሄ ማለት 350 በመቶ ሃገሪቱን በጀት የሚሸፍነው ዲያስፖራው ወገናችን ነው፡፡

_

*<u>በኢትዮጵያ ከውጭ የተላከ ገንዘብ/ የውጭ ሐዋላ ከ 2000 እስከ 2015 እኤአ</u> በ 2000 እኤአ 53 ሚሊዩን ዶለር የነበረው እያደገ መሄዱን የብሄራዊ ባንክ ገዥ ይፋ አድርረው ነበር፡፡ በግምት አንድ ሚሊዩን ከሚሆኑት ባህር ማዶ ሃገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሰደተኛች በ 2012 እኤአ 2.4 ቢሊዩን ዶለር ከውጭ ሐዋላ ወደ ሀገር ውስጥ እንደገባ የብሄራዊ ባንክ ገልፆል፡፡ በዚህም መሠረት ከባህር ማዶ ከሚኖሩ ኢትዬጵያውያን ወደ ሃገር ውስጥ የተላከ ገንዘብ የዓለም ባንክ ባወጣው መረጃ፣ ከሠንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው ዝቅተኛ ከውጭ ሐዋላ የተገኘው ገቢ በ 2001 እኤአ 18 ሚሊዩን ዶለር የነበረ ሲሆን ከፍተኛ 3 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር በ 2013 እኤአ እድረት እንዳሳየ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም በ 2015 እኤአ 4 ቢሊዩን ዶላር ወደ ሃገር ቤት ገንዘብ ልከዋል፡፡ በዚህም መሠረት በውጭ የሚኖሩ ኢትዬጵያውያን ወገናቸውን በመርዳትና በማስተዳደር የሲሶ መንግስትነት ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛሉ ሰለዚህም* በሀገራቸው ጉዳይ ከማንም በላይ ሊያገባቸውና ድምፃቸውም ሊሰማ ይገባቸዋል፡፡

Inward Remittances, Ethiopia 2000-2015

| Year | 2000 | 2001 | 2002 | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Remittances (USD Million) | 53 | 18 | 33 | 46 | 134 | 174 | 172 | 358 |
| % | | -15 | 183 | 139 | 291 | 130 | 99 | 208 |

| Year | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Remittances (USDMillion) | 387 | 262 | 345 | 371 | 2.4 Billion | 3 Billion | 2 Billion | 4 Billion |
| % | 108 | 68 | 132 | 107 | 647 | 125 | -67 | 200 |

Sources: Extracted from: The World Bank (2012) Remittances Data-inflow.

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ከውጭ የሚላከው ገንዘብ/ የውጭ ሐዋላ ከመጠን በላይ ቀንሶል፡፡ በባህር ማዶ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የህወሓት የግፍ አገዛዝ በመቃወም የሃዋላ እቀባ በተሳካ መልክ በማካሄድ ላይ ናቸው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ በወልቃይት ጉዳይና ከዲያስፖራው ወገን ጋር በመጣላት በእራስ ላይ መርዛማ ኮብራ መጠምጠምዎን ይወቁ እንላለን፡፡ የወያኔን ሥርዓት ከመውደቅ የሚያድን ምድራዊ ኃይል የለም፡፡ በሃገሪቱ ኢንቨስትመንት እየተዳከመ ሄዶ ቀዝቅዞል፣ ሜጋ ፕሮጀክቶች ቆመዋል፣ ፋብሪካዎች በውጭ ምንዛሪ እጦት ከአቅም በታች ይሰራሉ፣ ወዘተርፈ፤ የውጭ ምንዛሪ የለም፣ የነዳጅ፣ የመድኃኒት፣ የኬሚካል፣ የፋብሪካ ግብዓቶች መግዣ፣ የሸቀጣ ሸቀጦች ዎጋ የዋጋ ግሸበት ጣራ ነክቶል፡፡ የቱሪዝም ዘርፍ ገቢ መቀዛቀዝ፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ምክንያት የባህር ማዶ ጎብኝዎች ቁጥር መቀነስ፣ የሆቴሎች የመኝታ ቤትና ምግብ ገቢ መቀነስ፣ የአስጎብኝ ድርጅቶች ገቢ መቀነስ የመሳሰሉት ምልክቶች ይታያሉ፡፡ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ዴሬክተር አቶ ሞገስ ባልቻ የፖለቲካ አለመረጋጋቱን ምክንያት በማድረግ ግብር ያለመክፈል፣ ኪሳራ ወይም ዜሮ ሪፖርት የማድረግ ሰፊ ተግባር መስተዋሉን፣ በዚህም የተነሳ መንግሥት ገቢ መቀነሱንና ውጪ ኮንትሮባንድ በተለይም የገንዘብ ዝውውር በ 200 በመቶ መጨመሩን ለፓርላማው ሪፖርት አድርገዋል፡፡ ይሄ ማለት የውጭ ምንዛሪ ዶላር፣ ዩሮ፣ ፓውንድ ወዘተ ገንዘብ በ 200 በመቶ በኮንትሮባንድ ከሃገር ውጪ በወያኔ ሹሞችና የጦር ጀነራል መኮንኖች እንደሚወጣ ተጠቁሞል፡፡ በህገውጥ መንገድ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ምርቶች ወርቅ፣ ሠሊጥ፣ ቡና፣ የቁም እንሰሳቶች ወደ ሱዳን፣ ሱማሌ፣ ኬንያና ጅቡቲ በዶላር እንደሚሸጡ ተረጋግጦል፡፡ የመንግስታዊ ዘርፍ በግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ጣልቃ

መግባት የኢፈርት፣ ሜቴክ፣ ጥረት፣ ዲንሾ፣ ወንዶ የመሳሰሉ የህወሓት/ኢህአዴግ የፓርተ የንግድ ድርጅቶች በህግ ተወግደው ሳይመክኑ፣ የኮንትሮባንድና ህገወጥ የድንበር ንግድ ሳይከስም ፣ አድሎና ያልተገባ የንግድ ውድድር ሳይቀር፣ የንግዱ የሙስና ሠንሠለት ሣይበጣጠስ የውጭ ምንዛሪ ማሳደግ አይቻልም፡፡ ዳክተር አብይ አህመድ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ከብክነት በፀዳ መልክ መጠቀም፣ በውጭ ካሉ ኢትዮጵውያን የሚላከውን ማበረታታት፣ ጥቁር ገበያን ማስቀረት፣ የውጪ ምንዛሪ ገቢ የሚያስገኙ የግብርና ምርቶች ላይ በአግባቡ መስራት ይገባል ብለዋል፡፡ የባለሃብቱ ከአገር ብር ማሸሽ ተጠቃሽ የምንዛሪ እጥረት ምክንያት መሆኑን እንዲመልሱ ተማፅነዋል፣ በዚህ መንገድ የዲስፖራውን የስብዓዊ መብት ጥያቄ አትግደሉ፣ አትሰሩ የነፃነትና መብት ጥያቄ ሳይመልሱ ዶላሩን መመኘት ያሳፍራል፡፡ ሰው ሰው ያልሸተተ ልማት፣ የእናቶችን እንባ አያብስም፡፡

*ለህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት 25 ሸህ ህጻናትን በጉዲፈቻ ስም የሸጠ ከነዚህ ውስጥ 7000 ህጻናቶች የት እንዳሉ እናቶቻቸው የማያውቁበት የማፍያ ወንጀለኛ ያሉበት ሃገር ነው የምንኖረው፡፡* ዶክተር አብይ አአህመድ ሙስና ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ ችግር በሂደት እንደሚፈቱ ተናግረዋል ሂደት ማለት ጊዜ መግዣ የወያኔ ከንቱ ሃሳብ ነው፣ የዋናው አዲተር በሙስና የወንጀላቸውና በህዝብ ተወካዬች ምክር ቤት የቀረበውን ክስ በተግባር ማዋል የአንተን ቆራጥ አመራር ይጠይቃል፡፡ በሙስና የተዘፈቁ የብሄራዊ ባንክ ገዥዎችን ከሥራ ማሰናበትና አዲስ የባንክ የገንዘብ አቅርቦት ብድር ችግር ፖሊሲ አጥንቶ ተግባራዊ ማድረግና መፍታት፣ የአገልግሎትና ፍትህ አሰጣጥ ችግሮች መፍታት፣ ህዝብን ያላማከረ የመሬት አቅርቦት ችግር ለመሥራት አይታሰብ የሃገሪቱን የመሬት ፖሊሲ ከመንግሥት ኃብትነት ወደ ግል የህዝብ ኃብትነት መቀየር ብቻ ነው መፍትሄው፣ የግል ባለሃብቱ  ግብር በአግባቡ የሚከፍልና ማህበራዊ ሃላፊነትን እንዲሠራ የሚበረታታው ዘለቄታዊ እድገት በግልፅነት፣ በተጠያቂነት፣ ሲሠራ ብቻ ነው፡፡ የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግሥት፣ ዲያስፖራ ወገኖቻችንን ለሃገራቸውና ህዝብ  እንዳይሰሩ በማሰር፣ በመሰለል ተግባር ላይ በመጠመድ በጠባብ ብሄራዊ ስሜት አገር እየፈራረሱ ይገኛሉ!!!>> *ከዲያስፖራ ወገኖቻችን ወያኔ በእስራት ለሚያሰቃያቸው ዜጎችና የአገር ቤት ዜጎች እንዲፈቱ እንታገል!!!* የህወሓት የጦር አበጋዞች መንግስት ዲያስፖራ ተቃዋሚ ፖለቲከኛችን የህዝብ ልጆችን እያደኑ በመግደል ታሪክ ይቅር የማይለው አረመኔዊ ተግባር ፈፅመዋል፡፡ ከየመን ታፍኖ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የአርበኞች ግንቦት ሰባት ዋና ፀሃፊ፣ አቶ አንድአርጋቸው ፅጌ በአስቸኮይ እንዲፈታ ህዝብ ይጠይቃል፡፡ ለስብሰባ ከመጡት የዲያስፖራ ፖለቲካኞች አቶ አበራ የማነአብ ለአስራ አምስት ዓመታት በግፍ በመለስ ዜናዊ ሴራ ታስሮ መፈታቱን ልብ ይበሉ፡፡ ወ/ሮ ገነት ግርማና ሌሎቹም ታሪክ ያስታውሳቸዋል፡፡ ዲያስፖራው የህክምና ሰው ዶክተር ፍቅሩ ማሩ የልብ ህክምና ሆስፒታል ገንብተው ወገኛቸውን በማገልገል ላይ እያሉ በግፍ ታስረው እስካሁን በወህኒ ቤት በግፍ ይሰቃያሉ፡፡ ከጋምቤላ ቱወት ፖል ቢፈቱም ሌሎችም የጋምቤላ እሰረኛች፣ የወልቃይት እስረኞ፣ የትግራይ አረና እስረኖች፣ የኦሮሚያ የኦነግ እስረኞች ወዘተ እስካሁን አልተፈቱም፣ከኦጋዴን አብዲከሪም ሼህ ሙሴ ሌሎችም ዲያስፖራ የፖለቲካ ሰዎች በሃገራቸው እየተሰቃዩ ይገኛሉ፣ይፈቱ እንላለን! ህወሓት መቀሌ እስር ቤት ውስጥ ታስረው የነበሩትን ጺጋዬ ገብረመድህን፣ጎዶቹን መግደላቸውን ዘንግተዋል፣ ጊዜ ያወጣዋል፡፡ በኤች አር 128 መጽደቅ ለሃገራችን ስብአዊ መብቶች መከበር፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓተ ምህዳር መስፋትና አንባገነናዊ አገዛዝ ማክተም ያበስራል!!!

{1} *<u>የባህር ማዶ ልማት ትብብር (O</u>DA፡ Official Development Assistance) ከ 1991 እኤአ እስከ 2012 እኤአ ለህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት አርባ ቢሊዩን ዶላር የልማት እርዳታ ሰጥተዋል፡፡ በአለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ በአማካኝ በአመት ሁለት ቢሊዩን ዶላር እርዳታ ሃገሪቱ እንዳገኘች ያስረዳል፡፡ የባህር ማዶ ልማት ትብብር እርዳታ ከ 2008 እስከ 2015 እኤአ ያለውን ብቻ ብናይ ከ 3 እስከ 4 ቢሊዩን ዶላር ሃገራችን የልማት እርዳታ አግጥታለች፡፡ በኦዲኤ ዋና ዋናዎቹ እርዳታ አድራጊ መንግስቶችና ተቆማት አሜሪካ መንግሥት፣ የእንግሊዝ መንግሥት፣ የአውሮፓ ህብረት ኢንስቲቲዉሽኖች፣ ኢንተርናሽናል ዲቨሎፕመንት አሲስታንስና ግሎባል ፈንድ ናቸው፡፡*

የህወሓት/ ኢህአዴግ ፋሽስታዊ መንግሥት ለሦስተኛ ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ> እንዲያነሳ ጫና እንዲደረግበት የዲያስፖራው የትግል እንቅስቃሴ በነዚህ አገሮችና ድርጅቶች ላይ ማነጣጠር ይኖርበታል፡፡ ወያኔ የተነቃነቀ በትረ ሥልጣኑን ዴሞክራሲን በማፈን፣ ስብዓዊ መብቶችን በማፈን፣ ህገ-መንግስቱን በመጣስ የኢትዮጵያ ህዝብን አፍኖ በመግዛት ላይ መሆኑን በሠላማዊ ሠልፍ መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡ የህወሓት መንግሥትን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ> የወያኔ አንባገነን ስርዓት መገለጫ በመሆኑ የባህር ማዶ ልማት ትብብር ኢጋር አገራቶች  ድጋፍ ይቀንሳል ብሎም ይቆማል፡፡ በኢትዩጵያ የወያኔ ልማታዊ መንግሥት> ስም የወያኔ መንግሥታዊው ዘርፍ(ኢፈርት ሜቴክ፣ ኢዛና፣ ጥረት፣ ዲንሾ፣ ወንዶ ወዘተ) የግሉን ዘርፍ ኃብትና

ሊሠራ የሚችለውን ኢንቨስትመንት ሥራ ሁሉ በመሻማት የግሉን ዘርፍ እድገትና ሚና በመላ ሃገሪቱ አጨናግፎታል፡፡ የወያኔ ኢፈርት ኢንተርፕራይዞች፡- በወያኔ ባለሥልጣኖች የሚተዳደሩ የሜቴክ ድርጅቶች የሙስና መፈልፈያዎች፣ የእውቀትና የብቃት ችግር የተንሠራፋባቸው፣ በሥልጣን በመጠቀም የግል ፍላጎት ተጠቃሚነትን የሚያስፋፉ፣እንዲሁም ከለላን የሚያበረታቱ፣ የፖለቲካና የዝምድና አሰራር የነገሰበቸው ናቸውና ለቀጣዮ ትውልድ የሥራ ዕድል ሊፈጥሩ አይችሉም፡፡ በሃገሪቱ 30 ሚሊዮን ወጣቶች ሥራ አጥ ናቸው፡፡ ወጣቶች በሃገራቸው ሠርተው መኖር መብት አላቸው፡፡ አድሎዊና ተመጣጣኝ ያልሆን የክልሎች እድገት ይወገድ!! በክልላችን የሚካሄድ የመሬት ቅርምት ይቁም!! በክልላችን ኃብት የዘረፉ ለፍርድ ይቅረቡ! ያለ ኢኮኖሚ ነፃነት የፖለቲካ ነፃነት የለም! ወጣቶች የሚሉት ለዚህ ነው፡፡ የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ የኢህአዴግ መንግሥት ያወጣውን <<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ>> ተቃወመ የህዝቡን የመሰብሰብና ሃሳብ መግለጽን መከልከልን፣ የዴሞክራሲዊ መብቶችን የመጻፍ፣ መናገር፣ መደራጀት፣ የሠላማዊ ሰልፍና ስብሰባ ማካሄድና መሰረታዊ መብቶች ክልከላ መፍትሄ አይሆንም በማለት ምክረ ሃሳባቸውን አካፍለዋል፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት በሃገሪቱ ዴሞክራሲን ማስፈን፣ የምጣኔ ሃብት እድገት ማስመዝገብ፣ ለህዝቡ ብልፅግና ሰላምና መረጋጋት ያመጣል እንጂ የስድስት ወር <<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ>> ማወጅ መፍትሄ አይሆንም በማለት ኮንነዋል፡፡ እንዲሁም የአውሮፓ ህብረት አገራቶች የኢህአዴግ መንግሥት ያወጣውን <<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ> ተቃውመዋል፡፡ ኤችአር 128 በአሜሪካ ምክር ቤት ፀደቀ!!! የአውሮፓ ህብረትም ይቀጥላል፡፡ የዲጅታል ቴክኖሎጅ ወጣት ትውልድ የዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት፣ በሃገሪቱ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ለመመስረት የብዙሃን ፓርቲዎች የውድድር ሥርዓት ዘርግቶ፣ በህዝብ ድምፅ አሸናፊው ሥልጣን የሚይዝበት የምርጫ ስርዓት-አሥተዳደር ህወሓት/ ኢህአዴግ መንግሥት እንዲያመጣና ስብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ኤች አር 128 ያስገድዳል፡፡

{2} <u>ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት </u>(Foreign Direct Investment Inflows) <<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ>> ለሃገሪቱን የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚያስከትለው ጉዳት በተመለከተ በሃገሪቱ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት ይቀንሳል፡፡ ሰላም በሌለበት ሃገር የባህር ማዶ ኢንቨስተሮችን አይስብም፣ እንዲያውም ያፈሰሱትን ምዋለንዋይ ሸጠው ለመውጣት ይገደዳሉ፡፡ በሃገራችን የኢኮኖሚ ነፃነት ከሚገለፅባቸው ዋና ዋና መርሆዎች ውስጥ አንዱንም አታሞላ፡፡ አንደኛው የህግ የበላይነት፣የፍትህ ሥርዓት መከበር፣የንብረት ባለቤትነት መብት መከበር፣ የመንግሥት ሙስናን ለመዋጋት ያለው አቅም የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ የሃገር ውስጥና የባህር ማዶ ኢንቨስተሮች የህግ ሉዓላዊነት ያለበት ሃገር መዋለ-ንዋያቸውን አፍሰው በነፃነት ኃብት ማፍራት ይሻሉ፡፡ ህግና ፍትህ ባለበት ሃገር ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንት ፍሰት ከአመት አመት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ በኢትዮጵያ ህግ የለም፣ ፍትህና ርትህ አይሠራም፣ የዜጎች ንብረት የማፍራት መብት የለም፡፡ በኢትዮጵያ የህወሓት መንግሥት በሞኖፖል የተያዙ ንብረቶችና ኃብቶች መካከል፡-በሃገሪቱ የመሬት ኃብት የህወሓት መንግሥት በመሆኑ የግብርና፣የማኑፋክቸሪንግና አገልግሎት ዘርፍ ክፍለ ኢኮኖሚ እድገቱ የቀጨጨ ለመሆን በቅቶል፡፡ ህዝባችን የመሬት ኃብት ንብረት የመያዝ መብትና ነፃነት ስለሌለው በርሃብ አለንጋ ይሰቃያል፡፡ ህዝቡን መመገብ የማይችል መንግሥት ህዝቡን መግዛት አይችልም፡፡

በሃገሪቱ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት በ2008 እኤአ (109 ሚሊዮን ዶላር)፣በ2009 እኤአ (211 ሚሊዮን ዶላር)፣በ2010 እኤአ (288 ሚሊዮን ዶላር)፣በ2011 እኤአ (627 ሚሊዮን ዶላር)፣በ2012 እኤአ (279 ሚሊዮን ዶላር)፣በ2013 እኤአ (1281 ቢሊዮን ዶላር)፣በ2014 እኤአ (2132 ቢሊዮን ዶላር)፣በ2015 እኤአ (2168 ቢሊዮን ዶላር)፣2016 እኤአ (አልተገለጸም)፣ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት ነበር፡፡<<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንት ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንት ፍሰት በጣም ይቀንሳል፡፡>>

{3} <u>የባህር ማዶ ጎብኘዎች </u>በኢትዮጵያ የጎብኘዎች ቁጥር ይቀንሳል በዚህም ምክንያት ከቱሪስቶች የሚገኝ ገቢ ያሽቆለቁላል፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ይቀንሳል፣ በ2008 እኤአ ኢትዮጵያን የጎበኙ ቱሪስቶች ቁጥር 383 ሽህ ሲሆን ከዘርፍ 355400 ሚሊዩን ዶላር ገቢ ተገኝቶ ነበር፡፡ የቱሪዝም ዘርፍ አስተዋፅኦ ለአጠቃላይ አገር ውስጥ ምርት(ጂዲፒ) 10.4 በመቶ እንዲሁም ለሥራ ዕድል 6.3 በመቶ አበርክቶ ነበር፡፡ በ2014 እኤአ 770 ሽህ ጎብኘዎች ወደ ሃገራችን መጥተው ነበር፣ በ2015 እኤአ 717 ሽህ ቱሪስቶች መጡ (በ60 ሽህ ቀነሰ) በ2016 እኤአ 491 ሽህ ሃገር ጎብኘዋች መጥተው ነበር(279 ሽህ ጎብኘዎች ቁጥር ቀነሰ)፡፡ ከ2008 እስከ 2009 ዓ/ም ወያኔ <<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ> አውጆ የነበረበት ዓመታት መሆኑን ልብ ይበሉ፡፡ ከ2008 እስከ 2009/2010 ዓ/ም በኦሮሚያና አማራ ክልሎች በተነሳ ህዝባዊ አመፅ የሃገር ውስጥ የባህር ማዶ ኢንቨስተሮች ንብረት የሆኑ ፋብሪካዎችና እርሻዎች መውደም ምክንያት የታቀደው አልተሞላም፡፡<<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ>>

የውጭ ንግድ ገቢ አሽቆለቆለ፣ በአንጻሩ የገቢ ንግድ ወጪ በማደጉ የንግድ ሚዛኑ ተናግቶል፡፡ በዚህም የተነሳ ያልተረጋጋ የብር ምንዛሪ ተመንና የውጭ ምንዛሪ ክምችት እጥረት፣ የመንግሥትና የልማት ድርጅቶች በዕዳ ክፍያ ጫና ተከስቶል፡፡ በአጠቃላይ የአገሪቱ የፋይናንስና የባንክ ኢንዱስትሪው ልማቱ የሚጠይቀውን ፋይናንስ የማቅረብ ብቃት ወድቆ ነበር፡፡ በሃገሪቱ የፋይናሻል ዘርፍ ውድቀትና ኪሣራ ደርሶባቸዋል፡፡ በሃገሪቱ ኢኮኖሚ የዋጋ ግሽበቱንና የኑሮ ውድነቱን አባብሶታል፣ የውጪ ንግድ ገቢ በድርቅ ተመቶል፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት በጣም ተባብሶል፣ በእጥረቱ ምክንያት የኮንስትራክሽን ስራዎች በአብዛኛው ተቆርጠዋል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በርሃብ፣በድህነት፣በበሽታ፣በስደትና በጦርነት አዙሪት ቀለበት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በሃገሪቱ ውስጥ የፖለቲካ መረጋጋት አለመኖር፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አለማበብ፣ የመልካም መሪዎችና መልካም አስተዳደር እጦት፣ የስራ አጦች ብዛት፣ ገበያ መር የኃብት አጠቃቀም አለመኖር፣ የረዥም ግዜ  ኢንቨስትመንት እቅድ አለመኖር፣ የተትረፈረፈ ምርቶች ለውጭ ንግድ አለማምረት፣ የውጭ ምንዛሪ እጦት እንዲሁም የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚክ ስርዓት ዘላቂ ያልሆነ፣ ፊሲካልና ከዓለም አቀፍ ንግድ የውጭና የገቢ ንግድ የተዛባ የንግድ ሚዛን ኪሳራ መሆን በችግር ቀለበት ውስጥ እንድትሽከረከር ያደርጋታል፡፡ የኦሮሞ ቄሮ፣ የአማራ ፋኖ፣ የደቡብ አቦሸማኔ (የጉራጌ ዘርማ)፣ የሰሜኑ አናብስት!!! ጥያቄዎች ይመለሱ!!! ወጣት የነብር ጣት!!! >> ሳይፀድቅ የተጫነብንን  <<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ>> በብሄራዊ ትግላችን አናነሳዋለን፡፡ የወጣቶች መሬት አንቀጥቅጥ የ 3 ቀን የቤት መቀመጥ ትግል፣የገበያ አለመሳተፍ አድማ፣ የትራንስፖርት መኪኖች አድማ፣ የነዳጅ አመላላሽ ቦቴ አድማ በሃገር አቀፍ ደረጃ እንዲጠራ ኢሣት፣ የኦሮሞ ሚድያ ኔት ወርክ እንዲሁም ልዩ ልዩ የቴሌቪዝንና ሬድዮ  አገልግሎቶች፣ የተለያዩ በይነ-መረብ ድረገፆች  ጥሪውን በማድረስ ተባበሩ የአድማውን ቀነ ቀጠሮ  አሳውቁ እንላለን፡፡ ህብረ ብሄራዊ የቤት መቀመጥ አድማ ለማድረግ የሁሉንም ህዝብና ወጣቶች ያሳተፈ ትግል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከኢኮኖሚ ግንባታ በፊት የዴሞክራሲ ነፃነት ይቅደም!!! የአጋዚ ጦር ለፍርድ ይቅረብ!!! ሁለተኛና ሦስተኛ ዜጋ ሆነን መኖር እስከመቼ ድረስ!!!  ነፃነታችን እናስመልስ፣ ክብራችንን እናስመልስ! መሬታችንን እናስመልስ!!! የህሊና እስረኞች ይፈቱ!! የወያኔ እስር ቤቶች በዓለም ዓቀፍ ስብአዊ መብት ኮሚሽን ይጎብኙ!!! <<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ>> በህዝብ ትግል ይነሳል!!! ያለ ኢኮኖሚ ነፃነት የፖለቲካ ነፃነት የለም!!! ዳክተር አብይ አህመድ <<የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ>> አስነሳ!!! ወያኔ ጦር ህዝብ አይግደል!!! የሰው ነፍስ አያጥፋ!!! ግድያ ይቁም!!! ገዳዩች ለፍርድ ይቅረቡ!!! አንድ ለሥልጣን ብለናል!!! የኤች አር 128 መፅደቅ እንደግፋለን!!!

ድል ለዲያስፖራ ሲሦ መንግሥት የኤች አር 128 መፅደቅ ተጋድሎ ላደረጋችሁ ወገኖቻችን እድሜ ይስጣችሁ!!!
የሃገራችን ህዝብ ተርቦ፣ የወያኔ መንግሥት በወር 150 ሽህ ዶላር (በ18 ወራት 2.7 ሚሊዮን ዶላር ለአማላዩቹ ከፍሎም ተሸንፎል!!!